# ፋና የአማራ ልዩ ኃይልና ሚሊሻን ተጋድሎ መጥቀስ እያቃረረው ነው

በትናንትናው ዕለት የመከላከያ ሰራዊቱና የአማራ ልዩ ኀይል የአላማጣውን ድል አስመልክቶ መግለጫ ሰጥተው ነበር። ይሁንና ፋና የመከላከያውን ብቻ ነጥሎ ሰራው። ዋልታ የሁለቱንም ሰርቶታል።

ቅሬታ ቀርቦበት ይሁን እንጃ ፋና ቆይቶ የአማራ ልዩ ኃይልን ሳይጠቅስ ስለ መከላከያ ብቻ የሰራውን ዜና አንስቶታል። ማድረግ የነበረበት ዜናውን ማንሳት ሳይሆን፣ ከመከላከያ ጋር ዋጋ እየከፈለ ያለውን የአማራ ልዩ ኀይልን ጉዳይ አካትቶ ማስተካከል ነው።

ሆኖም ዜናውን አንስቶ በመከላከያ ብቻ ሌላ ዜና ሰርቷል። ይህ የሚያሳየው ፋና የአማራ ልዩ ኀይልን ተጋድሎ ለማንሳት ቃር ቃር እያለው እንደሆነ ነው።
መከላከያ ክህደት ሲፈፀምበት ደርሶ፣ ዋጋ ከፍሎ የትህነግን ኃይል እየተጋፈጠን ያለ የአማራ ኃይል መግለጫ ቆርጦ ማውጣት፣ ተጋድሎውን መደበቅ ሌላ ክህደት ነው!
ስትለጥፉ ስታነሱት፣ ስትቆርጡ ስትቀጥሉ የማንከታተል መስሏችሁ ከሆነ ስህተት ነው። በደንብ እንከታተላለን!

**Getachew Shiferaw**

20/11/2020